CHILD CARE RESOURCES

# የመዋለ ሕጻናትን መምረጥ - ለወላጆች የዝርዝር መግለጫ

(ይህን ገጽ ኮፒ ያድርጉና እያንዳንዱን አቀራቢ በሚጎበኙ ጊዜ ይዘው ይሂዱ)

የአገልግሎት አቀራቢው ስም ______________________ የአገልግሎት አቀራቢው ስልክ ቁጥር ______________

## የሥራ ፈቃድ/የሥራ ምስክር ወረቀት

*በዝምድና ለማይገናኙት ልጅ በመደበኛ መልክ የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት የሚያቀርብ ማንኛው ሰው ከዋሽንግተን ስቴት የሕብረተሰብና ጤና አገልግሎት ጽ/ቤት (ዲኤስኤችኤስ) የሥራ ፈቃድ ማግኘት አለበት። የሥራ ፈቃዱ የሚያመለክተው ዲኤስኤችኤስ ያወጣቸውን መሠረታዊዎቹን አስፈላጊ ነጥቦች ፕሮግራሙ እንደሚያሟላ ነው። የሥራ የምስክር ወረቀቱ የፈቃደኝነት ፕሮግራም ሲሆን አገልግሎት አቀራቢዎች ፕሮግራሞቻቸው የብሔራዊውን የሥራ ጥራት ደረጃ እንደሚያሟሉ የሚያሳዩበት የሥራ ማሳያ ያዘጋጃሉ።*

- ❏ ማዕከሉ/ቤቱ የሥራ ፈቃድ አለው? ከሥራው ፈቃድ ግዴታ ነፃ ነው? (ለምሳሌ፣ የግማሽ ቀን ቅድመ ትምህርት ቤት፣ የመንግሥት ወኪል መሥሪያ ቤቶች ወዘተ)
- ❏ ማዕከሉ/ቤቱ የሥራ ምስክር ወረቀት አለው? (ኤንኤኢዋይሲ፣ ኤንኤኤፍሲሲ ወዘተ)

## ሠራተኞች

*በአንድ አዋቂ ሰው ጥበቃ እንዲደረግላቸው የሚፈቀደው የልጆች ቁጥር በሥራ ፈቃዱ ደንቦች የተወሰነ ነው። ጥበቃ የሚያደርጉት ሰዎች በሚደናሩ ጊዜ ከልጆች ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ተተኪ የሚሆን በቂ ሰው ፕሮግራሙ እንዳለው ያረጋግጡ።*

- ❏ ለልጁ ጥበቃ የሚያደርጉ በቂ ሠራተኞች/አዋቂ ሰዎች አሉ?
- ❏ ጠባቂው ምን የሥራ ልምድና የትምህርት ደረጃ አላቸው? ለተከታታይ ትምህርት ዕቅድ አለ?
- ❏ የሥራ ባልደረቦቹ ተስማሚና በሥራ ተባባሪዎች ናቸው? ፈጥኖ ደራሽና ረጂዎች ናቸው?
- ❏ ሠራተኛው/ጠባቂው በማዕከሉ ወይም ቤቱ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ ሠርተዋል?
- ❏ ጠባቂው ወቅታዊ የሆነ የመጀመሪያ እርዳታ/ሲፒአርና ኤችአይቪ/ኤድስ ስልጠና አላቸው?
- ❏ ሠራተኞች የሚያገለግሉዋቸውን ቤተሰቦች ባህል፣ የብሔረሰብ፣ የሃይማኖትና የአኗኗር ልዩነቶችን ያከብራሉ እንዲሁም ዋጋ እንዳለው ይቆጥሩታል?
- ❏ ሠራተኞቹ ከተለያየ የልጆች ምድብ ጋር ለመሥራት አስፈላጊ የሆነ ሙያና ዕውቀት አላቸው?

## የሠራተኛ/ልጅ ግንኙነት

- ❏ ሠራተኞች ከልጆች ጋር ግንኙነታቸው እንዴት ነው? ሠራተኞቹ ልጆች በራሳቸው እንዲተማመኑ የሚያበረታቱ ይመስላል?
- ❏ የማየው ምን ዓይነት የሥራ ግንኙነት ነው?
- ❏ በልጆች መካከል የሚፈጠረውን አለመግባባት አገልግሎት አቀራቢው የሚፈታው እንዴት ነው?

## የፕሮግራሙ አካባቢ

- ❏ በቂ ስዕሎች፣ ብሎኮች፣ የአሻንጉሊት የሙዚቃ መጫወቻዎች፣ መጫዎቻዎችና ዕንቆቅልሽ(ፐዝል) ወዘተ አሉ?
- ❏ የማያቸው ተግባራት ለልጁ የዕድሜ ምድብ ተገቢ የሆነ ነው?
- ❏ ልጆቹ ደስተኛና ናቸው?
- ❏ የፕሮግራሙ ይዘት በማህበረተሰቡ ውስጥ የሚገለገሉትን ቤተሰቦች የባህል፣ የብሔረሰብ፣ የሃይማኖትና የአኗኗር ልዩነቶች ያንፀባርቃል ደሞስ ዋጋ እንዳለው ይቆጥራል?
- ❏ ፕሮግራሙ የልጁን የቤት ልምድና ቋንቋ ዋጋ እንዳለው ይቆጥራል ያከብራል?
- ❏ የሚቀርቡት ዝግጅቶች የልጁን ልዩ ፍላጎት እንዲያሟሉ ሆነው መዘጋጀት ይችላሉ?
- ❏ ለተለያዩ ዝግጅቶች በየጊዜው የሚመደብ ጊዜ አለ?
    - ❏ የቤት ውስጥና የውጭ ጨዋታ?
    - ❏ የሸለብታና የእረፍት ጊዜ? (ዕድሜያቸው ለትምህርት ቤት ከደረሱ ልጆች በስተቀር)
    - ❏ የኪነ ጥበብና የሙዚቃ ችሎታ መግለጫዎች?
    - ❏ የማስመሰል ጨዋታ?
    - ❏ የሚቀመስና ምግብ?
    - ❏ ጉዞዎችና ልዩ ዝግጅቶች?
    - ❏ የማንበብና ተረት ማጫወት?
    - ❏ የቤት ሥራና የጥናት ጊዜ? (ዕድሜያቸው ለትምህርት ቤት ለደረሱ ልጆች)
- ❏ ለእያንዳንዱ ዝግጅት በቂ ቦታ አለ?
- ❏ በመዋያው ቀን ወቅት ቴሌቪዥን ስለመመልከት የፕሮግራሙ ፖሊሲ ምንድን ነው?
- ❏ የአካባቢው ሁኔታ ለልጆች በአካል መጎልመስ የሚያበረታታ ነው?

## የወላጅ ተካፋይነትና የወላጅ/አገልግሎት አቀራቢ ግንኙነት

*የዋሽንግተን ስቴት ሕግ ልጆች በመዋለ ሕጻናት ጥበቃ ላይ እያሉ በወላጆቻቸው/በአሳዳጊያቸው በግለጽ ጉብኝት እንዲደረግላቸው ፈቃድ እንዲሰጡ*

*የመዋለ ሕጻናት ፕሮግራሞችን ይጠይቃል።*

- ❑ ፕሮግራሙ የተለያዩ ዓይነቶች የወላጅ ተካፋይነት እንዲኖር ያበረታታል?
- ❑ አሳሳቢ ጉዳዮችንና ጥያቄዎችን የማሳውቀው እንዴትና ለማን ነው?
- ❑ ከልጄ ጠባቂ ጋር በየጊዜው መነጋገር እችላለሁ?

## የሥራ ቀደም ተከተሎችና ፖሊሲዎች

*የዋሽንግተን ስቴት እያንዳንዱ የሥራ ፈቃድ ያለው የመዋለ ሕጻናት አገልግሎት አቀራቢ ፖሊሲዎችንና የሥራ ቀደም ተከተሎችን የሚያስረዳ የወላጆች ማስታወሻ ደብተር እንዲኖረው ይጠይቃል።*

- ❑ የወላጅ ማስታወሻ ደብተር አለ? የሚከተሉትን ያጠቃልላል?
- ❑ የመግቢያ አስፈላጊ ነጥቦች/የመመዝገቢያ ቀደም ተከተሎች?
- ❑ የሥራ ሰዓቶችና የየቀኑ ዝግጅት የሥራ ምድብ
- ❑ በነፃ አገልግሎት ለማግኘት ፈቃድ?
- ❑ ባሕርይን መቆጣጠርና ማረም?
- ❑ የመጓጓዣና የመስክ ጉዞ ቀደም ተከተል?
- ❑ ሕክምና/ለታመሙ ልጆች የእንክብካቤ ቀደመ ተከተል?
- ❑ የክፍያ መጠንና የአከፋፈሉ ሁኔታ?
- ❑ ምግብና የሚቀመስ?
- ❑ ልጅ ሲጎሳቆል ስለማሳወቅስ?
- ❑ ልዩነት የማያደርግ ቃል?
- ❑ ሃይማኖታዊ ዝግጅቶች?
- ❑ ለትንንሽ ልጆች እንክብካቤ ቀደም ተከተል?
- ❑ ዳይፐር፣ ብርድ ልብስ፣ መኝታ የሚያቀርበው ማን ነው?

## ጤናና ደህንነት

- ❑ የድንገተኛ ጊዜ ስልክ ቁጥሮችና ቀደም ተከተሎች በግለጽ ተለጥፈዋል?
- ❑ ሠራተኞች የድንገተኛ መርጃ ዕቃው ያለበትን ያውቃሉ? ሊደረስበት የሚችልና የተሟላ ነው?
- ❑ ማዕከሉ/ቤቱ ንጹሕና ምስቅልቅል የሌለበት ነው?
- ❑ ለእሳት አደጋ ጊዜ ለመዘጋጀት ልምምዶች በየጊዜው እየተደረጉ ይመዘገባሉ? የሳት አደጋ ጊዜ መውጫዎች መተላለፊያ ተዝግቷል?
- ❑ የእሳት አደጋው የመውጫ ፕላን ተለጥፏል?
- ❑ የውጭ መጫዎቻ ሥፍራው ከአደጋ የተጠበቀ ነው? አደጋ ከሚያደርሱ ነገሮች ነጻ ነው? ታጥሯል?
- ❑ ማዕከሉ/ቤቱና ሌሎቹ መገልገያ ዕቃዎች ከአደጋ የተጠበቁና በደንብ የተጠጉ ናቸው?
- ❑ ለተፈጥሮ አደጋ ጊዜ ዕቅድ አለ ደሞም ፕሮግራሙ ለልጄ በመሬት መንቀጥቀጥ ጊዜ የመርጃ ዕቃዎች አሉት?
- ❑ ልጅን በማድረሻና በመውሰጃ ጊዜዎች ላይ የሚደረጉ የፀጥታ ጥበቃ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? ያልታወቁ ሰዎች የሚወገዱበት እንዴት ነው?

## አጠቃላይ አስተያየት

- ❑ ደንቦቹ ምክንያታማና ግልጽ ይመስላሉ?
- ❑ የሌሎቹ ልጆች ባሕርይ የሚስማማዎት ነው?
- ❑ ቦታው ለልጅዎ ተስማሚ የሚሆን ይመስላል?
- ❑ ልጅ ቢሆኑ ኖሮ እዚህ ደስተኛ ይሆኑ ነበር?
- ❑ ልጅዎን እዚህ ትተ መሄዱ የማያሰጋዎት ነው?
- ❑ ልጄ እያደገ/ች ጊዜ በሚመጣ/በምትመጣ ጊዜ ፕሮግራሙ ፍለጎቱን/ቷን ያሟላል?

## መሠረታዊ መረጃዎች

- ❑ ምግቡና የሚቀመሰው ተገቢና ጤናማ ነው
- ❑ መጓጓዣ አለ
- ❑ ለምግብና መጓጓዣ ተጨማሪ ክፍያ አለ
- ❑ የመዋለ ሕጻናቱ የሥራ ፈቃድ በግልጽ ይታያል?
- ❑ የስነ ስርዓት መመሪያው ከእኔ መመሪያ ጋር ተመጣጣኝ ነው?
- ❑ የሽንት ቤት አጠቃቀም ስለጠናው ከእኔ ጋር ተመጣጣኝ ነው?

## የመዋለ ሕጻናት የሥራ ፈቃድ

*የመዋለ ሕጻናት ፕሮግራሙን ከጎበኙ በኋላ ስለተወሰኑ መረጃዎችና ሊመርጡት ስላሰቡት አገልግሎት አቀራቢ ሊኖሩ ስለሚችሉ የስሞታ ታሪክ ለማወቅ ለስቴቱ የሕብረተሰብና ጤና አገልግሎት ጽ/ቤት ሊደውሉ ይችላሉ። ፈቃድ ሰጪውን ለማግኘት 206-721-6941 ይደውሉ ወይም http://www-app2.wa.gov/dshs/trial/occp/Reg4a/find_licensor.htm ይመልከቱ። የአገልግሎት አቀራቢው ሙሉ ስምና የዚፕ ኮድ ያስፈልግዎታል።*

**ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ እርዳታ ለማግኘት እባክዎን ይደውሉልን።**

206-329-5544 ወይም በኦንላየን www.childcare.org

CHILD CARE RESOURCES